# መግቢያ

የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) ከመጋቢት 29 እስከ ሚያዝያ 6 ቀን 1998 አራተኛ ጠቅላላ ጉባዔውን አካሂዶ ይህንን የፖለቲካ ፕሮግራም እንደገና በማሻሻል አፅድቆ አውጥቷል:: ይህ ፕሮግራም የኢሕአፓን አቋዋሞችና መሰረታዊ ዓላማዎችን የሚያንፀባርቅ ነው::

ኢሕአፓ ከተመሠረተበት ከሚያዝያ 1964 ዓ.ም. ጀምሮ የኢትዮጵያ ሕዝብ በነፃና ርትዓዊ ምርጫው ዴሞክራሲያዊ መንግስትን እንዲመሠርትና መብቱም ተከብሮ ሉዓላዊነትዋ የተጠበቀች ሀገሩን በሁሉም መስክ ለመገንባት እንዲችል ታግሏል:: ኢሕአፓ ሶስት ልዩ ልዩ አገዛዞችን ከሕዝብ ጎን ሆኖ የታገለው እነዚህ አገዛዞች የሕዝብን መብት ረግጠው ጨቋኝ ሥርዓቶችን ስለመሠሩትና መሠረታዊ ለውጥ ለማምጣትም ዝግጁነት የሌላቸው ሆነው በመገኘታቸው ነው:: መሬት ለአራሹ፣ ዴሞክራሲ ለጭቁኑ ህዝብ፣ የሀገር ሉዓላዊነት ይከበር፣ አንድነት በዴሞክራሲና በእኩልነት መሠረት ላይ ይረጋገጥ፣ ፍትህና የህግ የበላይነት ይስፈን ወዘተ እያለ ኢሕአፓ ከፍተኛ መስዋዕትነትን ከፍሎ ለሕዝብ የገባውን ቃል ኪዳን በማክበር ታግሏል:: በዚህም ረጅም የትግል ሂደት ድርጅቱ በትግል ከትግል እየተማረ ፣ ከስህተቱ ተምሮና ታርሞ፣ ጠንካራ ጎኑን በይበልጥ አጠናክሮ፣ ተጨባጩ ሁኔታን በማጤንም ፕሮግራሙን እያሻሻለና እያስተካከለ በፅናት ቀጥሏል:: አራተኛው ጉባዔውም ዛሬ ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ በመመርመር እስከዛሬ ይሠራበት በነበረው የፖለቲካ ፕሮግራም ላይ አስፈላጊውን ማሻሻያ አድርጎ እነሆ አቅርቧል::

ዛሬ በሥልጣን ላይ ያለው ገዥ ሃይል በጠባብ ብሄርተኛነት የተቀየደና ሕዝብን በብሄረሰብ ደረጃ ከፋፍሎና አናክሶ ሊገዛ ይሁነኝ ብሎ የወሰነ ፀረ ኢትዮጵያ ቡድን ነው:: ይህ ቡድን በሥልጣን ላይ ያለው በሕዝብ ድጋፍ ሳይሆን በኃይሉ ተመክቶ ተቃውሞን እያፈነ በመቀጠል ነው:: በግንቦቱ 1997 ምርጫ ደግሞ ሕዝብ አሁን ያለውን አገዛዝ ከቶም እንደማይፈልገው በምርጫው ወቅት ድምፁን በመንፈግ ያረጋገጠው ጉዳይ ቢሆንም አገዛዙ ጉልበቱን ተጠቅሞ ሕዝብን በመጨፍጨፍ ዛሬም እየተንገዳገደ በሥልጣን ላይ እንደቀጠለ ይገኛል:: ይባስ ብሎም የፖለቲካ ተቃዋሚዎችን÷ የነፃው ፕሬስ ጋዜጠኞችን÷ ለመብታቸው የታገሉ ብዙ ሺ ዜጎችን ለእስር ዳርጎ፣ ነፃ ጋዜጦችንም ዘግቶ በአምባገነንነቱ ሊገፋበትም ወስኖ እየተጓዘ ያለ በመሆኑ ሕዝብ ተባብሮ በሁለገብ ትግል ይህን አገዛዝ ሊያስወግድ ይገባል ብሎ ኢሕአፓ ያምናል:: ለዓመታት በኢትዮጵያ የፖለቲካ



መድረክ ዋና ወይም አቢይ ሆነው የቆዩ ጥያቄዎች አሁንም መፍትሄ የሚሹ ናቸው:: ዛሬም የመፍትሄ ያለህ ይላሉ :: ሰርቶ አደሩ ሕዝብ በተለይ÷ የኢትዮጵያ ሕዝብ በአጠቃላይ የአምባገነናዊ አገዛዝ ሰለባ ሆኖ በመሰቃየት ላይ ነውና ይህን አገዛዝ በትግል ማስወገድ የሁሉም ዜጋ ተቀዳሚ ግዴታ ሆኖ ቀርቧል:: በልዩ ልዩ ጊዜም ይህ አገዛዝ እንዲለወጥ፣ የሕዝብን ድምፅ እንዲያከብርና የሰላምና ዕርቅን መንገድ እንዲመርጥ ጥሪ ተደርጎለት ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ በአምባገነንነቱ የቀጠለ መሆኑም ዛሬ አለምንም ጥርጥር ግልፅ የሆነ ጉዳይ ነው::

ኢሕአፓ ለብዙሀኑ መብት ሲታገል የቆየ ድርጅት እንደመሆኑ መጠን በአሁኑ ወቅትም ቢሆን ዴሞክራሲ ሲል ለብዙሀኑ የሚጠቅም ዴሞክራሲን ማለቱ ነውና በማህበረሰባዊ ወይም ሶሻል ዴሞክራሲ የፖለቲካ አስተሳሰብና መርሆዎች መመሪያነት ነው ትግሉን እየቀጠለ ያለው:: ኢትዮጵያ ከገባችበት የድህነትና የመከራ ማጥ መውጣት የምትችለው በሁሉም ዜጎቿ ጥረትና ትግል በመሆኑም ድርጅቱ በዚህ ፕሮግራም ውስጥ በተካተቱት መሰረታዊ አቅዋሞች ዙሪያ ሕዝብን አሰባስቦ ለማታገል ጥረቱን ቀጥሏል:: ዘላቂ ሕዝባዊ ድልን ለማረጋገጥ ደግሞ ከሌሎችም ማበር አስፈላጊ በመሆኑ በቅድሚያ በሕዝብ ደረጃ የህብረት ግንባር ፖለቲካን በማራመድ የከፋፋዩን አገዛዝ ሴራ ለማክሸፍም ይታገላል:: ባለፉት 15 ዓመታት የአገዛዙ ምንነትና ማንነት ፍዳ እየተቀበለ ያለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከእንግዲህ በአረመኔዎችና ጨቋኞች ላይገዛ ተነስቷልና ኢሕአፓ በታሪክ እንዳስመሰከረው ዛሬም ከሕዝብ ጎን ቆሞ ለአገዛዙ መወገድ፣ ለዴሞክራሲ ስርዓት መስፈን ይታገላል:: ሀገርን ለማዳንና መብትን ለማስከበር ለሚደረገው ትግል ሕዝቡ እየተደራጀ እንዲታገል፣ እየታገለም በይበልጥ እንዲደራጅ ጥሪውን ሲያስተላልፍም በቅድሚያ የራሱን ፅናትና ትግል ቀጣይነትም በገቢር እያስመሰከረ ነው::

ትግላችን ይቀጥላል!

የኢትዮጵያ ሕዝብ በጠላቶቹ ላይ ድልን ይቀዳጃል!

እናቸንፋለን!

# የኢሕአፓ የፖለቲካ ፕሮግራም

## አንቀጽ፡-፩

**መሠረታዊ ዓላማ፤**

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሉዓላዊነትና የሥልጣን ምንጭነት በሕግ የሚረጋገጥበት፣ በእኩልነት ላይ የተመሠረተ የሕዝብና የአገር አንድነት የሚጠበቅበት፣ የእምነትና የሀሳብ ነፃነት የሚከበርበት በሕዝብ ነፃና ርቱዓዊ ምርጫ የሚቋቋም ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መመሥረት::

## አንቀጽ፡-፪

**የሀገሪቱ ህገ መንግሥታዊ መሠረትና የህዝብ ይሁንታ፤**

1) የሀገሪቷ ሕገ-መንግሥት ሁሉም የፖለቲካ ኃይሎች፣ የተለያዩ የኅብረተሰቡ ክፍሎችና ወኪሎች፣ የሙያ ማኅበራት ተጠሪዎች፣ የሃይማኖት መሪዎች፣ የሕግ አዋቂዎች፣ የሀገር አዛውንቶች፣ ታዋቂ ግለሰቦች (በታሪክ፣ በኪነት፣ በሳይንስ፣ በሌሎችም ዘርፎች ወዘተ) በሚሳተፉበት ሕገ-መንግሥታዊ ጉባዔ ይረቀቃል::

2) በሕገ-መንግሥቱ ረቂቅ ላይ ሕዝቡ በነፃና በስፋት ተወያይቶበት፣ የጎደለ ካለ ጨምሮ፣ የሚቀየረውን ቀይሮ፣ የሚሻሻለውን አሻሽሎ፣ በመጨረሻም ሰነዱን በውሳኔ ሕዝብ ያጸድቃል::

3) በሕገ-መንግሥቱ መሠረት በሕዝቡ ነፃና ርቱዓዊ የሆነ ጠቅላላ ምርጫ የሚቋቋመው መንግሥት የሥልጣን ዘመኑ የተወሰነ ይሆናል::

4) ሕገ-መንግሥቱ የሚከተሉትን ዐበይት ሀሳቦችና መተክሎች ማካተት ይኖርበታል ብሎ ኢሕአፓ ያምናል፣ ይህ እንዲሳካም ይታገላል::

ሀ. ሕግ አውጪው፣ የሕግ አስፈፃሚውና የዳኝነት ሰጪው



መንግሥታዊ ዘርፎች ሥልጣናቸው፣ ኃላፊነታቸው ተግባራቸው በግልጽ ተለይቶ እንዲዋቀሩ፤

ለ. በሕዝብ ነፃና ርቱዓዊ ምርጫ የሚቋቋመው ምክር ቤት (ሕግ አውጪ ዘርፍ) ባለ ሁለት ክፍሎች (ባይ ካሜራል) እንዲሆንና አንደኛው ክፍል የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በአስተዳደር አካባቢዎች የሕዝብ ብዛት ላይ የሚመሠረት፣ ሁለተኛው ክፍል በፌዴራል የብሔረሰብ ስብጥር ላይ ተመሥርቶ ሁሉም ብሔረሰቦች በእኩል የሚወከሉበት እንዲሆን፣ የሁለቱም ክፍሎች አባላት በቀጥታ በሕዝቡ የሚመረጡ እንዲሆኑ፤

ሐ. የሕዝቡ ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶች በዝርዝርና በግልጽ እንዲሰፍሩ፣ እንዲረጋገጡ፤

መ. የብሔረሰቦች እኩልነትንና የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነትን፣ ጂኦግራፊያዊና ኢኮኖሚያዊ ትስስርን መሠረት ባደረገ ፌዴራላዊ አሀዶች ግንኙነት ላይ የተዋቀረ የአካባቢ አስተዳደር (ራስገዝ) መብትን የሚያረጋግጡና የሚገልጹ አንቀጾች እንዲሰፍሩ፤

ሠ. ዴሞክራሲ የሚረጋገጥበት የፖለቲካ ሥርዓት እንዲመሠረት፤

ረ. በሕዝቡ ነፃና ርቱዓዊ ምርጫ የሚቋቋመው ዴሞክራሲያዊ መንግሥት የሥልጣን እድሜ በአራት ዓመት እንዲወሰን፤

ሰ. የኢትዮጵያ ሀገራዊ ሉዓላዊነትና ድንበሮችዋም የማይደፈሩና የማይገሰሱ መሆናቸው በሕገ-መንግሥቱ ውስጥ እንዲሰፍር፤

ሸ. ኢትዮጵያዊ የዜግነት መብት የተከበረ የማይደፈርና የማይገፈፍ መሆኑም እንዲረጋገጥ፤

## አንቀጽ፡-፫

**የሽግግር ወቅት፤**

1) በሽግግሩ መንግስት ለመሳተፍ ፈቃደኛ ከሆኑ የፖለቲካ ኃይሎች፤ የህረተሰቡ ወኪሎች፣ ከሙያ ማህበራት ተጠሪዎች፣ ከህገር ሽማግሌዎች፣ ከታዋቂ ግለሰቦች፣ ወዘተ

የተውጣጣ የሽግግር መንግስት አቋቁሞ በሀገር አቀፍ ምርጫ ለሚቋቋመው መንግስት ምሥረታ ጥርጊያ ማዘጋጀት

2) ሀ. በሽግግሩ ወቅት የሁሉም የፖለቲካ ኃይሎችና የኅብረተሰብ ወኪሎች መንግሥታዊ ተሳትፎ በስምምነት በመመካከር፥ በአቻነት መንፈስና በዴሞክራሲያዊ ግንኙነት ላይ የተመሠረተ ይሆናል።

ለ. በሽግግሩ ወቅት ሁሉም የፖለቲካ ኃይሎች በሰላማዊ መንገድ ፕሮግራማቸውን ለሕዝቡ ለማስተዋወቅ ዕድሉ ይኖራቸዋል።

ሐ. የሽግግሩ መንግሥት ዕድሜ ከሦስት ዓመት የበለጠ አይሆንም።

3) የሽግግሩ መንግስት ማኅበራዊ፥ ኢኮኖሚያዊ ወዘተ ፖሊሲዎችን በዴሞክራሲያዊ መንገድ በሽግግሩ ምክር ቤት ተወካዮች የሚወሰን ሲሆን የሀገሪቷን ሕልውና በሚነኩ ወሳኝ ጉዳዮች ላይ የሽግግር መንግሥቱ የመወሰን መብት/ሥልጣን ፍጹም የለውም።

4) ሀ. በሽግግሩ መንግሥት ከሚሳተፉት የፖለቲካ ኃይሎች ታጣቂዎችና እነዚሁ ኃይሎች በሚስማሙባቸው መመዘኛዎች መሠረት

- በፈቃደኝነት በውትድርና ከሚቀጠሩ ዜጎች የተውጣጣ፥ ታዛዥነቱ ለሽግግሩ መንግሥት የሆነ፥ የሀገሪቷን ሕላዌና ድንበሮች የሚጠብቅ፥ ሀገራዊ መከላከያ ኃይልና
- ጸጥታን የሚጠብቅ የፖለቲካ ወገንተኝነት የሌለውና ሙያተኛ የሆነ የፖሊስ ኃይል

ይቋቋማሉ።

ለ. የተጠቀሱት የሽግግር ወቅት ሀገራዊ መከላከያ ኃይልና የፖሊስ ኃይል እንደተቋቋሙ በተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች የተቋቋሙትና በእነሱም የሚመሩት የታጠቁ ኃይሎች፥ ቡድኖች ወዘተ በሙሉ ይፈርሳሉ።

5) ሀ. የሽግግሩ መንግሥት በሽግግሩ ወቅት የሕዝቡን ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶች የማክበርና የማስከበር ኃላፊነትና ግዴታ ይኖርበታል።



ለ. የሽግግሩ መንግሥት መዋቅርና ይዞታዊ ስብጥር በተሳታፊዎቹ ስምምነት የሚወሰን ይሆናል።

## አንቀፅ:-፬

## መሰረታዊ ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶች፤

ወደፊት በምትመሠረተው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ ውስጥ የሁሉም ዜጋ ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶች አለገደብ እንዲከበሩ ማድረግ፤

1) የ ግግርና የጽሑፍ ነፃነት፥ ሰላማዊ ሰልፍና የሥራ ማቆም አድማ የማድረግ፥ የሥራና የመኖሪያ ቤትን የመምረጥና የመቀየር፥ በሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭ የመጓጓዝ፥ ከመንግሥት ጣልቃ ገብነት ነፃ በሆኑ የሙያ/የብዙኃን ማኅበራት የመደራጀት፥ የፖለቲካ ድርጅት የማቋቋም፥ ወይም በተቋቋሙት ውስጥ አባል የመሆን፥ የመምረጥና የመመረጥ፥ ንብረት የማፍራትና የግል ንብረት ባለቤት የመሆን፥ ቋንቋንና ባሕልን የመጠበቅና የማሳደግ ወዘተ መብቶችን ማክበር።

2) ሃይማኖትን ከመንፈሳዊ እምነት ውጪ በፖለቲካ ፍልስፍናነትና መመሪያነት እስካልተጠቀመ ድረስና የዘር የበላይነትን መሠረት እስካላደረገ ድረስ ማንኛውም ድርጅት ሕጋዊ ሕልውና ኖሮት በሰላም የመንቀሳቀስ መብቱን ማስከበር።

3) በሕገ-መንግሥቱ የሚደነገገውን ከመንግሥት ጣልቃ ገብነትና ቁጥጥር ነፃ የሆነ ሥርዓት በተግባር እንዲውል ማድረግ፤ የሕግን የበላይነት ማረጋገጥ፤ ሁሉም ሰው በሕግ ፊት እኩል መሆኑን ማረጋገጥ፤ አለፍርድ ቤት ትዕዛዝ ማንም ሰው ከ48 ሰዓት በላይ በማረፊያ ቤት እንዳይቆይና እንዳይታሰር፤ መኖሪያ ቤቱ እንዳይፈተሽ፤ ጥፋተኛነቱ በፍርድ ቤት እስካልተበየነ በመከሰሱ ብቻ ንጹሕነቱ እንዳይሻር፤ በዋስ የመለቀቅ መብቱ እንዲከበርለት፤ ጠበቃ እንዲቆምለትና ከጠበቃውም ጋር የመገናኘት መብቱ እንዲጠበቅለት፤ ያለፍርድ ቤት ብያኔ የ ብረት ባለቤትነት መብቱ እንዳይደፈር፤ ስልኩ እንዳይጠለፍ፤ ፖስታው እንዳይከፈት፤ አለፈቃዱ ንብረቱ የመንግሥት መገልገያ እንዳይሆን… ወዘተ ማድረግ።

4) ሁሉም ዓይነት ኢሰብዓዊ ቅጣት የተከለከለ ይሆናል፡፡ ኢሰብዓዊ ቅጣትን የሚፈጽሙ በሕግ እንዲጠየቁ ማድረግ፡፡

5) በዘር፥ በብሔር/ብሔረሰብ ፥ ወይም በፆታ ወይም በሃይማኖት ልዩነት ላይ ተመሥርቶ ማበላለጥ ወይም ማዳላት በሕግ እንዲከለከል ማድረግ፡፡

6) ማንኛውም እድሜው 18 ዓመት የደረሰ ዜጋ የመምረጥ መብት፤ እድሜው 25 ዓመት የሞላው ዜጋ ደግሞ የመመረጥም መብት ጭምር ያለው መሆኑን ማረጋገጥ፡፡

## አንቀጽ፡-፭

**የብሔረሰቦችን የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት ማስከበር፥ እኩልነታቸውን ማረጋገጥ፤**

1) የብሔር/ብሔረሰቦች የራስን በራስ የማስተዳደር፥ በቋንቋቸው የመጠቀምና ባሕላቸውን የማዳበር መብታቸው እንዲከበር ማድረግ፡፡

2) በእኩልነት ላይ ለተመሠረተ የሕዝቦች አንድነት መታገል፡፡

3) በሀገሪቱ የፖለቲካ፥ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ሕይወት ውስጥ በሚኖራቸው ተሳትፎ፥ በማንኛውም ብሔረሰብ ላይ አድልዎ አለመኖሩን ማረጋገጥ፡፡

4) ሆኖም በኢኮኖሚ በትምህርት በጤና፥ ወዘተ ረገድ ለተጎዱ ወይም ለተረሱ ክፍሎች ልዩ ድጋፍ መስጠት፡፡

## አንቀጽ፡-፮

**መንግሥትና ሃይማኖትን መለየት፤**

1) ሁሉም ሃይማኖቶች በሚከተሏቸው ምዕመናን ድጋፍና ርዳታ መንፈሳዊ ተልዕኳቸውን የሚያሟሉ ይሆናሉ፡፡

2) መንግሥት በሃይማኖት ጉዳይ ሃይማኖት በመንግሥት ጉዳይ ጣልቃ አይገቡም፡፡



3) በአማኞች ላይ የሚደረገውን ተጽዕኖ ማስወገድ፡፡ የሁሉንም ዜጋ የዕምነት ነፃነት ማስከበር፡፡

## አንቀጽ፡-፯

**ብሔራዊ ኢኮኖሚን መገንባት፤**

1) ብሔራዊ ብልጽግናን መሠረት ያደረገ፥ የሀገሪቷንና የሕዝቦቿን ጥቅም ያካተተና ቅድሚያ የሰጠ፥ በገበያ ኢኮኖሚ መርሕ ላይ የተመሠረተ ብሔራዊ ኢኮኖሚ መገንባትና የሕዝቡን የኑሮ ደረጃ ማሻሻል፡፡

2) በግብርና መስክ

ሀ) የግብርናው ክፍል ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የደም ሥር እንደመሆኑ መጠን ይህን ክፍለ ኢኮኖሚ ለማዳበርና ለማሳደግ በሁሉም መስክ መጣር፡፡

ለ) አርሶ አደሮች በሚያርሱት መሬት ላይ የባለንብረት መብት ማለትም የመሸጥ የመለወጥ የማውረስ በዋስትና (በወለድ አግድ) የማስያዝ ወዘተ ያላቸውን መብት ማክበር፡፡

ሐ. መሬት አልባ አርሶ አደሮች በኅብረተሰቡ ስምምነትና ድጋፍ የሚታረስ  መሬት በንብረትነት የሚያገኙበትን መንገድ መሻት፡፡

መ. ሰፋፊ ዘመናዊ እርሻዎችን ለማቋቋም ለሚሹና ለሚችሉ በግብርና ለሚተዳደሩ ግለሰቦች መንግሥት መሬት በረጅም ጊዜ የይዞታ ውል (በኮንሴሽን) ይሰጣል፡፡ የሚሰጠውን መሬት መጠንና የይዞታውን ውል (የኮ ሴሽኑን) ሁኔታ በሕግ ማስወሰን፡፡

ሠ. መንግሥት የአርሶ አደሩ የኑሮ ደረጃ ከፍ እንዲልና ምርቱም እንዲዳብር ለአርሶ አደሮች አስፈላጊውን ዕርዳታና አገልግሎት (ምርጥ ዘሮች፥ ማዳበሪያ፥ የሰብል ተባይ መከላከያ፥ የግብርና መሣሪያዎችን ወዘተ) ከቀረጥ ነፃ ማቅረብ፥ ገንዘብ ከእርሻ ብድር አገልግሎት (ባንክ) የሚያገኙበትን ሁኔታ መፍጠር፥ መጋቢ መንገዶችን፥ ትምህርት ቤቶችን፥ ክሊኒኮችን፥ የዕደ-ጥበባዊ ትምህርት አገልግሎትን፥ የመስኖ ግድቦችንና ቦዮችን ስራና ግልጋሎት ፥ የጉድጓድ ውሃዎችን ወዘተ…ማስፋፋት እንዲሁም

ማዳበሪያን ሊተኩ የሚችሉ የግብርና የምርምር ዘዴዎችን ማበረታታትና በግብር እንዲውሉ ማድረግ፡፡

ረ. በከፊል ወይም በሙሉ ዘላን የሆኑትን የኅብረተሰብ ክፍሎች ከሥፍራ ወደ ሥፍራ እየተዘዋወሩ በሚቆዩባቸው አካባቢዎች መርዳት፥ ከተቻለም በእነሱ ፈቃደኝነት ላይ ተመሥርቶ ለእነሱ አመቺ በሆኑ ቦታዎች እያሰፈሩ በግብርና ሊሰማሩ ወይም በዘመናዊ መልክ የከብት እርባታ ሊያካሂዱ ወዘተ የሚችሉበትን ሁኔታ መፍጠር፥ የጤናና የትምህርት አገልግሎቶችን መስጠት፡፡

ሸ. ማንኛውም የፖለቲካ፥ የሰብዓዊ መብት ጠባቂና ግልጋሎት ሰጪ፥ የሲቪክ ወዘተ ድርጅት በግብርና፥ በኢንዱስትሪ፥ በንግድ፥ በትራንስፖርት፥ በባንክ፥ በፋይናንስና በመድኅን ወዘተ ተቋማት መስክ እንዳይሰማራ በሕግ የተከለከለ ይሆናል፡፡

3) በኢንዱስትሪ መስክ፡-

ሀ. የኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ በገበያ ኢኮኖሚ መርሕ መሠረት እንዲንቀሳቀስ ማድረግ፥ ማበረታታት፡፡

ለ. ለሀገሪቱ ብሔራዊ ጥቅም በጣም አስፈላጊ ሆነው በመገኘታቸው ወይም የግል ባለሀብቶች ሳይሰማሩባቸው ቀርተው በመንግሥት ቁጥጥርና አስተዳደር ሥር እንዲውሉ ከተደረጉት በስተቀር በኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ የግል ባለንብረትነት መብት እንዲከበር ማድረግ፥ በሀገር ውስጥ ያሉ ከበርቴዎች (ባለሀብቶች) በኢንዱስትሪው መስክ ተሳትፏቸው እንዲጠናከር መደገፍ /ማበረታታት፥ የተመጣጠነ የቀረጥ ሥርዓት በማውጣት የአገር ውስጥ እንዲስትሪዎችን መደገፍ፡፡

ሐ.የውጭ ሀገር ከበርቴዎች (ባለሀብቶች) ከሀገሪቱ የኢኮኖሚ ጥቅም ጋር በማይጋጭ መንገድ በሀገሪቷ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ እንዲሳተፉ፥ በተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎችና የሥራ መስኮች እንዲሰማሩ ማበረታታት፡፡

መ.ኢንዱስትሪዎችና ፋብሪካዎች በተወሰኑ አካባቢዎች ብቻ ሳይከማቹ ጥሬ ዕቃዎች በሚገኙባቸውና ሊያሠሩ የሚችሉ ሁኔታዎች ባሉባቸው በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች እንዲቋቋሙ ማበረታታትና መርዳት፡፡



4) ንግድን በሚመለከት፡-

ሀ. የሀገር ውስጥ ገበያን ለማስፋፋት፥ ነጋዴዎችን ለማበረታታት በልዩ ልዩ የሀገሪቷ የኢኮኖሚ ዘርፎች የሸቀጥና የምርት ልውውጥ እንዲዳብር ህግ ያወጣል አስፈላጊ ተቋሞችንና የልማት አውታሮችንም ይዘረጋል ፡፡

ለ. ወደ ሀገር የማስገባትና ወደ ውጭ የመላክን ንግድ በተመለከተ በዋናነትና በቀዳሚነት የሀገሪቷ የግል ባለሀብቶች ነፃ ሆነው እንዲሠሩ ማበረታታት፥ ድጋፍ መስጠት፡፡

ሐ. ለውጭ ንግድ የሚሆን ምርትን በገበያ ኢኮኖሚ መርሕ ላይ በመመሥረት ለማሳደግ የሚደረገውን እንቅስቃሴ ማበረታታት፡፡

መ. ሕገወጥ ንግድን ለማስወገድ አስፈላጊ የሆኑትን ተጨባጭ እርምጃዎች መውሰድ፡፡

ሠ. የተባበሩት መንግሥታት፥ የአፍሪካ ህብረት ድርጅት ወይም ሌሎች ኢትዮጵያ አባል የሆነችባቸው ዓለም አቀፍና አህጉራዊ ድርጅቶች ማዕቀብ ካደረጉባቸው ሀገሮች በስተቀር በእኩልነትና በጋራ ጥቅም ላይ የተመሠረተ ንግድ ከማንኛውም አገር ጋር እንዲካሄድ ማድረግ፡፡

5) ትራንስፖርትና መገናኛ በሚመለከት፡-

ሀ. ትራንስፖርትና መገናኛ ለገበያ መስፋፋት፥ ለአጠቃላይ ብሔራዊ ኢኮኖሚ ዕድገት እንዲሁም ለሕዝቦች ግንኙነትና ትሥሥር ብሎም ለሀገሪቱ አንድነት ማጠናከሪያ ከፍተኛ አስተዋጽዖ የሚያደርግ በመሆኑ ከፍተኛ ትኩረት መስጠት፡፡

ለ. መንግሥት መንገዶችን፥ የባቡር ሀዲዶችን፥ አውሮፕላን ጣቢያዎችን ወዘተ በመሥራት የባቡር የየብስና የባሕር ትራንስፖርት እንዲሁም የቴሌኮሙኒኬሽንና የፖስታ አገልግሎትን በመስጠት በዚህ ክፍለ ኢኮኖሚ የሚፈለገውን አገልግሎት እንዲሟላ ማድረግ፡፡

ሐ. በቅርብና በሩቅ የሕዝብና የዕቃ ማጓጓዣ ከፍተኛ ዕጥረት በመኖሩ መንግሥት በዚህ ሥራ ለሚሰማሩ ኢትዮጵያውያን አስፈላጊውን ማበረታታት ያደርጋል፡፡

6) የባንክና የመድኅን (ኢንሹራንስ) ድርጅቶች፡-

ሀ. ብሔራዊ ባንክን በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ማድረግ::

ለ. መንግሥት በየጊዜው በሚያወጣው ዝርዝር ሕግ መሠረት የግል ባለሀብቶች በመድኅንና በባንክ ሥራዎች እንዲሳተፉ ማድረግ:: የሚኖራቸውን ተሳትፎና ዝርዝር ሁኔታዎች በሕግ ማረጋገጥ:: ተሳትፎአቸው እንዲዳብር ማበረታታት::

7) የከተማ ቦታና ቤትን በሚመለከት:-

ሀ. ማንኛውም ሰው የከተማ ቦታን በግል ንብረትነት የመያዝ ቤት የመሥራት የማከራየት፥ የመሸጥ የመለወጥ፤ የማውረስ፤ በወለድ አግድ የማስያዝ መብቱ የተጠበቀ ነው::

ለ. የኪራይ ቤት እጥረትን ለመቀነስ መንግሥት አቅሙ በፈቀደለት ተገቢ እርምጃዎችን ለመውሰድ ይጥራል፥ ባለሀብቶች የሚከራዩ ቤቶች፥ የቁጠባ ቤቶች ወዘተ እንዲሠሩ ያበረታታል::

ሐ. የተወረሱ ቤቶችን በተመለከተ ከመንግሥትና ከባለንብረቶች የተውጣጣ ኮሚቴ ተቋቁሞ ጉዳዩ ተጠንቶ ብዙኃኑን የማይጎዳና የባለንብረቶችን ጥቅምም ያገናዘበ መፍትሔ እንዲሰጠው ደረጋል::

## አንቀጽ:-፰

<u>የሠርቶ አደሩን ሕዝብ ጥቅምና ደኅንነት ማስጠበቅ፤</u>

1) የሠራተኛ ማኅበራት ተወካዮችንም በማሳተፍ የሠራተኛ ሕግ ማውጣትና በሥራ ላይ ማዋል::

2) የሠራተኛውን የመደራጀት መብት ማስከበር፥ የሙያ ማኅበራትን ነፃነት ማስጠበቅ፥ የሠራተኞችን የሥራ ማቆም አድማ መብት ማስከበር፥ ከመንግሥትና ከግል ባለሀብቶች ጋር ለተሻለ የሥራ ሁኔታ፥ ለደመወዝ ጭማሪ፥ ለአደጋ ዋስትና፥ ለጡረታ አበል ክፍያ፥ ለነፃ ሕክምና ዋስትና ወዘተ የመደራደር መብታቸውን ማረጋገጥ::

3) ከ16 ዓመት በታች ዕድሜ ያላቸው ሕፃናት በፋብሪካዎችና በማዕድናት ውስጥ ተቀጥረው እንዳይሠሩ በሕግ መከልከል::



4) የሠራተኞች መደበኛ የሥራ ሰዓት በቀን ከ8 ሰዓት እንዳይበልጥና ሠራተኞች በሳምንት ለ48 ሰዓታት የማረፍ መብት እንዲጠበቅላቸው ማድረግ

5) ሠራተኞች በቂ የሆነ የሕመም፥ የሕክምናና የማህበር ተግባሮች መሳተፊያ የሥራ ፈቃድ እንዲሁም የዓመት ዕረፍት እንዲያገኙ ማድረግ፤ ሰራተኛ ሴቶች ከወሊድ በፊት የአንድ ወር ከወለዱ በኋላ የሁለት ወር የወሊድ ፈቃድ እንዲያገኙ ማድረግ::

6) የሠራተኞችን የመነሻ ደመወዝ የኑሮ ውድነትን ለመቋቋም በሚያስችል ሁኔታና በሀገሪቱ የኢኮኖሚ አቅምና በአሠሪዎችም ችሎታ ላይ ተመሥርቶ መወሰን፥ ከኑሮ ሁኔታ ጋር ማስተካከልና ማሳደግ::

7) ሠራተኛው ሥራ አልባ በሚሆንበት ጊዜ የሀገሪቷ አቅም በሚፈቅደው መሠረት ሊረዳበት የሚችልበትን መንገድ መሻት፥ ሥራ አጥነትን ለመቀነስ መጣር::

8) በልዩ ልዩ ምክንያቶች የተፈናቀሉና ለጉዳት የተዳረጉ ዜጎች ዕርዳታ የሚያገኙበትን መንገድ መፈለግ::

9) ተፈላጊው ሙያ ያላቸው የሀገሪቷ ዜጎች እስካሉ ድረስ የሥራ ቦታ በቅድሚያ ለኢትዮጵያውያን እንዲሰጥ ማድረግ::

10) የሀገሪቱ ዜጎች በረሀብ፥ በጥማትና እርዛት፥ በወረርሽኝ፥ በዘመኑ ቀሳፊ በሽታ (በኤይድስ) ፥ በወባ፥ እንዲሁም በመጠለያ እጦት የሚደርስባቸውን ጉዳትና አደጋ በማስወገድና በመከላከል በሕይወት የመኖር ዋስትና እንዲኖራቸው ከፍተኛ ጥረት ማድረግ::

## አንቀጽ:-፱

<u>ለሀገር ዕድገትና ብልጽግና የሚያገለግል የትምህርት ሥርዓት ማቋቋም፤</u>

1) ትምህርት ከአገሪቷና ከሕዝቧ ታሪክ ባሕልና ልምድ እንዲሁም ፍላጎት ጋር ተቀናጅቶ የሚራመድበትን መንገድ መፈለግ፥ ከምርት ሥራ እንዳይነጠል ማድረግ፥ መሃይምነትን ማጥፋት፥ ዕድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ

ሕፃናትን ለማስተማር በሕግ መደንገግና ተግባራዊ ማድረግ፡፡

2) በሥርዓተ ትምህርት ፕሮግራም ዝግጅት ላይ ልምድ ባላቸው ባለሙያዎች የተረቀቀና ሕዝቡ ማለትም መምህራን፥ ወላጆች፥ ተማሪዎች ተወያይተውበት የአጸደቁት ብሔራዊ የትምህርት ፖሊሲ በሥራ ላይ ይውላል፡፡

ሀ) የነፃ ትምህርት እንዲስፋፋ መጣር፡፡ የሙያና የቴክኒክ ት/ቤቶችን፥ የማታ ት/ቤቶችን፥ የክረምት ትምህርትንና ዩኒቨርስቲዎችን ማስፋፋት፡፡

ለ) በሀገሪቷ ክፍሎች የሚካሄዱትን ትምህርታዊ ዕቅዶች ማስተባበር፡፡

3) የትምህርት ዕድል ሳያገኙ ለቆዩ ክፍሎች የተለየ ትኩረት መስጠት፤ ብቃት እያላቸው በችግር ትምህርት ለሚያቋርጡ ድጋፍ ለመስጠት መጣር፡፡ ለተንቀሳቃሽ ከብት አርቢዎች ዜጎች ልጆችም ተስማሚ የትምህርት ግልጋሎት መስጠት፡፡

4) የአስተማሪዎችን የሥራ፥ የሥልጠናና የደመወዝ ሁኔታ ማሻሻል፥ መርዳት፥ የተመቻቸ የሥራ አካባቢና ሁኔታን ማረጋገጥ፡፡

5) የተማሪዎችንና የአስተማሪዎችን በነፃ የመደራጀት መብት መጠበቅ፥ ትምህርታዊ ተቋሞች ከመምህራንና ከወላጆች በተውጣጣ ኮሚቴ እንዲተዳደሩ ማድረግ፡፡

6) የቴክኒክ፥ የሳይንስ፥ የግብርና ወዘተ ትምህርትን ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ማስፋፋት፡፡ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ጥናትና ምርምር ለሚያደርጉ ተቋሞችና ሊቆች፥ ለኪነጥበባት ሰዎች፥ ለደራሲያን ወዘተ እርዳታ ማድረግ፡፡ ግኝቶችን፤ የፈጠራ ውጤቶችንና በሙከራ ላይ ያሉ የአዕምሮ ሥራዎችን የባለቤትነት መብት በህግ እንዲጠበቅ ማድረግ

7) መንግሥት ለሕፃናት የተለየ እንክብካቤ በማድረግ አቅሙ እስከፈቀደ ድረስ የአውደ ሕፃናትንና (መዋእለ ሕጻናት) የሕክምና አገልግሎት ተቋሞችን መቋቋም ያበረታታል፤ ይረዳል

8) የግል ትምህርት ቤቶች በሀገሪቷ ሕግ መሠረት በትምህርት ዘርፍ በበቂ (በስፋት) የሚሳተፉበትን ሁኔታ መፍጠር፡፡



## አንቀጽ ፡-፲

<u>ለሕዝብ የሚያገለግል የጤና ጥበቃ ሥርዓት ማቋቋም፤</u>

1) የሕዝቡን ጤና ለመጠበቅ የጤና አገልግሎትን በገጠርና በከተማ በሚገባ ማስፋፋት፤ በገጠር ክሊኒኮችን ማስፋፋት፤ ተላላፊ በሽታዎችን በተቀነባበረ ዘመቻና ክትባት ማጥፋት፤ የጤና ባለሙያዎችን በብዛት ማሰልጠን፡፡

2) አቅም ለሌላቸው ዜጎች ዕርዳታ ተደርጎላቸው በነፃ ሊታከሙ የሚችሉበትን መንገድ መሻት፡፡

3) ሀገራዊ የሕክምና ዘዴዎች መድሃኒቶች በሳይንሳዊ ጥናትና ምርምር እየተደገፉ በሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ፡፡

4) የግል ሐኪም ቤቶች፥ ክሊኒኮችና ሆስፒታሎች በሀገሪቷ ሕግ መሠረት በስፋት የሚሳተፉበትን ሁኔታ መፍጠር፤ ትክክለኛ ግልጋሎት መስጠታቸውን ማረጋገጥ፡፡

5) በሀገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች የሚወጡ የጤና አገልግሎት ዕቅዶችን በማጣጣም አገልግሎቶችንም ማስተባበር፥ መቆጣጠር፡፡

## አንቀጽ፡-፲፩

<u>በወንዶችና በሴቶች መሃከል የእኩልነትን መብት ማስከበር፤</u>

1) በፖለቲካ፥ በኢኮኖሚ፥ በማኅበራዊ ኑሮና በባሕል፥ በትምህርት፥ በጤና አገልግሎት ወዘተ በወንዶችና በሴቶች መሃከል እኩልነት እንዲኖር ማድረግ፡፡

2) ለተመሳሳይ ሥራ እኩል ክፍያን ማረጋገጥ፡፡

3) የሴቶች በማኅበር የመደራጀትን መብት ማስከበር፡፡

4) ለማኅበረሰብ ዕድገትና ነፃነት የሚስማሙ የጋብቻና የቤተሰብ ግንኙነት ሕጎችን ማውጣት፤ በዚሁ ሕግ በሚወሰነው መሠረት ለአቅመ ሔዋን እድሜ ያልደረሱ እንዳያገቡ ማገድ፤ ሴቶች ወሊድን ለመቆጣጠር ያላቸውን

መብት ማስከበር::

5) ሴተኛ አዳሪነትን ለማስቀረት ለሴትኛ አዳሪነት መስፋፋት ምክንያት የሆኑትን ሁኔታዎች ለማስወገድ መጣር÷ ለሴተኛ አዳሪዎች ትምህርትና ሥራን ለመስጠት መጣር::

6) በኢትዮጵያ ገጠሮች ውስጥ የሴቶችን ህይወት ለማሻሻል አስፈላጊ የሆኑት የመጠጥ ውሃ ቧንቧዎችን ወይንም ጉድጓዶችንና የመስኖ ውሃ ቦዮችን÷ የወፍጮ ተከላዎችንና የማገዶ አቅርቦቶችን ቅድሚያ መስጠት፣ የሴቶች መብት መከበሩን ማረጋገጥ::

## አንቀጽ:-፲፪

**<u>የተፈጥሮ ሀብትንና የአካባቢ ደኅንነትን መንከባከብ፣</u>**

1) የሀገሪቷ ወንዞች÷ ፏፏቴዎች÷ ሐይቆችና ኩሬዎች በሕዝብ ባለቤትነት በመንግሥት ቁጥጥር ሥር መሆናቸውን ማረጋገጥ::

2) የሀገሪቷን የተፈጥሮ ሀብትዋን ማለትም የደንዋን÷ የዱር አራዊትዋን÷ የአፈርዋን÷ የውሃዋንና የአየርዋን ንጽሕና መጠበቅ:: የሀገሪትዋ የተፈጥሮ ውበትና ጤናማነት እንዲጠበቅ ከብክለት ለመከላከል የሚያስችሉ እርምጃዎችን መውሰድ:: ሁኔታው በተባባሰባቸው አካባቢዎችም የተፈጥሮ ሚዛ ለመጠበቅና የአካባቢ ብክለትን ለመከላከል÷ የወንዞች÷ የጅረቶችን÷ ንጽሕናን ማረጋገጥ፣ የአፈር መሸርሸርን፣ የደን መመንጠርን÷ መጋየትን÷ ለመከላከል በመንግሥትና በሕዝብ ተሳትፎ ያላሰለሰ እርምጃ መውሰድ::

3) የተፈጥሮ ሚዛ በከፍተኛ ደረጃ ለተዛባበት አካባቢ የተለየ ትኩረት በመስጠት በሁኔታው ተጎጂ የሆነውን ሕዝብ ከተደጋጋሚ ረሀብ ለማዳን የተጠኑ እርምጃዎችን በሕዝብ ትብብር ተግባራዊ ማድረግ::

4) ለዱር አራዊት ጥበቃ የተከለሉ ዘመናዊ ፓርኮችን ማቋቋም÷ ተቋቁመው ያሉትን በአግባቡ መያዝ÷ ሕገወጥ አደንንና ዱር ምንጠራን የሚከላከል የዱር አራዊትና የደን ጥበቃ ኃይል/ተቋም መመሥረት::



5) ወንዞች ፏፏቴዎች÷ ሐይቆችና ኩሬዎች በዕቅድና በአግባቡ ተፈጥሮን በማይጎዳ (በማያዛባ) መንገድ ለኅብረተሰቡ ጠቀሜታ እንዲውሉ ማድረግ÷ የውሃ ኃይልና የኤሌትሪክ ማመንጫዎችን እንዲሁም ሌሎች የኃይል ማመንጫ ዘዴዎችን በማስፋፋት የደን ጭፍጨፋን ለማስወገድ መጣር::

6) የተፈጥሮ ሀብትንና የአካባቢ ደኅንነትን ከመጠበቅ አንፃር ደምብ አውጥቶ ይህንንም በባለ ኢንዱስትሪዎች ወዘተ እንዲከበር ማድረግ::

7) ለተፈጥሮ ሀብትና ለአካባቢ ደኅንነት ጥበቃ ወጪ ሆነ ለአጠቃላይ የገቢ ምንጭነቱም የሕዝባችንን ክብርና የሀገሪቱን ጥቅም በማይነካ መልኩ የጉብኝት ግልጋሎትን (ቱሪዝምን) ማበረታታት:: የሀገር ውስጥ ቱሪዝምን ማበረታታት፣ ለቱሪዝም መስፋፋት የሚሆኑ ቅድመ ሁኔታዎች (ሆቴሎች÷ መንገዶች÷ ወዘተ) እንዲሟሉ ለማድረግ መጣር::

8) ስለተፈጥሮ ሀብትና ስለአካባቢ ደኅንነት ጥበቃና አስፈላጊነት በሀገር አቀፍ ደረጃ ትምህርታዊ ዘመቻን ማካሄድ::

## አንቀጽ:-፲፫

**<u>የሀገሪቷን መከላለከያ ኃይል በተመለከተ፣</u>**

በሕገ-መንግሥት ውስጥ የሠፈሩትን የሕዝቡን መብቶች የሚያከብር፣ እንዲሁም የሕዝቡን ፍላጎቶችና ጥቅሞች የሚጠብቅ÷ የሀገሪቷን ድንበርና ሉዓላዊነት የሚከላከል የጦር ኃይልና የሕዝቡን ሰላምና ፀጥታን የሚያስከብር የፖሊስ ሠራዊት መመሥረት::

1. ማንኛውንም ኢትዮጵያዊ ያላገለለ አስፈላጊ መሥፈርቶችን በሚያሟላ መንገድ ተመልምሎ የተውጣጣ ታዛዥነቱም ለኢትዮጵያ ሕዝብና በሕዝቡ ለተመረጠ መንግሥት የሆነ ሙያተኛ ወታደራዊ ተቋም መመሥረት:: ለሀገር ውስጥ ሰላምና ፀጥታ ጥበቃም ታዛዥነቱ ለኢትዮጵያ ሕዝብና በሕዝቡ ለተመረጠ መንግሥት የሆነ ሙያተኛ

የፖሊስ ተቋም መመሥረት፡፡

2. የጦር ኃይሉና የፖሊስ ኃይሉም በውጼታቸው (በፍላጎታቸው መሠረት) በሚቀጠሩ የጦር/የፖሊስ ኃይሎች አባላት የሚቋቋሙ ይሆናል፡፡

3. የጦር ኃይሉና የፖሊስ ሠራዊቱ በፖለቲካው ውስጥ ጣልቃ እንዳይገቡ መደንገግ፡፡

ሀ. የጦር ኃይሎችና የፖሊስ ኃይል አባላት በሀገሪቷ የፖለቲካ ሕይወት ውስጥ ተሳትፎአቸው በመምረጥና በውሳኔ ሕዝብ በመሳተፍ ብቻ ይሆናል፡፡

ለ. በጦርና ፖሊስ ሠራዊቶች ውስጥ የፖለቲካ ኃይሎች እንቅስቃሴ የተከለከለ ይሆናል፡፡

ወታደሮችና ፖሊሶች የማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት/ቡድን/ስብስብ አባል ሊሆኑ አይችሉም፡፡

ሐ. በፖለቲካ ለመሳተፍ (የድርጅት አባል ለመሆን፥ ለመመረጥ) የሚፈልጉ የጦር ኃይሉና የፖሊስ አባሎች በቅድሚያ ከጦር ኃይሉ መልቀቅ/መሰናበት አለባቸው፡፡

4. የጦርና የፖሊስ ሠራዊቱን አባሎች ደኅንነት መጠበቅ፣ የጡረታ መብታቸውን ማስከበር፣ በግዳጅ ተሠማርተው ለተሰዉ መደበኛ ወታደሮችና ፖሊሶች ቤተሰቦች ተገቢ ዕርዳታና እንክብካቤ መስጠት፡፡

5. በኢትዮጵያ ውስጥ የውጭ ሀገር የጦር ሠፈሮች እንዳይቋቋሙ በጥብቅ መከልከል፥ የጦርና የወታደራዊ ጥገኝነትም እንዳይፈጠር ማድረግ፡፡

## አንቀጽ፡-፲፩

**<u>በገለልተኛነትና በሠላም ፈላጊነት ላይ የተመሠረተ የውጭ ፖሊሲ መከተል፣</u>**

1) የኢትዮጵያን ጥቅም በመጠበቅና በማስቀደም ላይ በመመሥረት በተባበሩት መንግሥታትና በአፍሪካ ህብረት/አንድነት ማዕቀብ ከተጣለባቸው ኃይሎች በስተቀር ከሁሉም የውጭ ሀገሮች ጋር በሠላም አብሮ መኖር፥ በእኩልነትና በጋራ ጥቅም መሠረት ግንኙነት መመሥረት፥



ማጠናከር፡፡

2) ከጎረቤት ሀገሮች ጋር በሰላም የአብሮ መኖርን መርሕ መከተል፡፡

3) ለአፍሪካ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ትሥሥር አንድነት ከሚታገሉ ኃይሎች፥ ድርጅቶችና ሀገሮች ጋር በመተባበር የአፍሪካ ህብረትን/አንድነትን የተለያዩ ዘርፎችን መደገፍ፡፡

4) ለፍትሕ፥ ለዴሞክራሲ፥ ለነፃነታቸውና ለሰብዓዊ መብት ለሚታገሉት ሕዝቦች ሁሉ የኢትዮጵያን ድጋፍ መግለጽ፡፡

---------//////---------